ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 47 ነሀሴ 15/2018 ዓ.ም

በውስጥ ገጾች

የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በ2019 በጀት ዓመት እቅድ ላይ ውይይት አካሄዱ
ገጽ 2

በስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል በ2018 በጀት ዓመት የላቀ ውጤት መመዝገቡ ተገለፀ
ገጽ 3

የፀረ-ሙስና ትግል በኢትዮጵያ ካለፉት ሁለት አስርታት
ገጽ 5

የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካለዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!

## የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የብር ኢዮቤልዩ ምስረታ በዓሉን አከበረ







የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ወይዘሮ ሎሜ በዶ በመድረኩ ላይ እንደገለፁት፣ ሙስናን በመታገል ረገድ በሀገራዊ ምክክር ደረጃ መግባባት ላይ መደረሱን ጠቁመው፤ አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ በማድረግና ህዝቡን ባለቤት ያደረገ የፀረ-ሙስና ትግል በማጠናከር ሌብነትን የሚጸየፍ ትውልድ መገንባት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የዲሞክራሲያዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቴ አለነ፣ ኮሚሽኑ ባለፉት 25 ዓመታት ያሳለፋቸውን ሦስት ዋና ዋና የዕድገት ምዕራፎች አብራርተዋል። ከ1993 እስከ 2000 ዓ.ም በምርመራና ክስ ላይ ያተኮረ እንደነበር፤ ከ2000 እስከ 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ግን ሙስና በስፋት የተንሰራፋበትና የኮሚሽኑ አቅም የተዳከመበት ወቅት እንደነበር አውስተዋል። ከ2010 ዓ.ም የለውጥ ወቅት ወዲህ ግን አገልግሎቶችን ከሰው ንክኪ ነፃ የሚያደርጉ አሰራሮችን በመዘርጋትና ህግ ማስከበር ላይ በትኩረት እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተቋቋመበትን 25ኛ ዓመት (ብር ኢዮቤልዩ) ምክንያት በማድረግ «የኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግልትላንት ለዛሬ፣ ዛሬ ለነገ» በሚል እሳቤ ያዘጋጀውን የምክክርና የግምገማ መድረክ በ በአዳማ ከተማ አካሂዷል።

ወደ ገጽ 2 የዞረ

## የኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ ተካሄደ

የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ተመሳሳይ ኮሚሽኖች ጋር በጋራ ያዘጋጀው የ2018 ዓ.ም ትስስር ጉባኤ የተካሄደ ሲሆን፣ በጉባኤውም የ2018 በጀት ዓመት የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና የ2019 በጀት ዓመት እቅድን አስመልክቶ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል።

ጉባኤው "አንድ እቅድ፣ አንድ ሪፖርት" የተባለውን አሰራር መሰረት በማድረግ የተከናወኑ ስራዎችን የገመገመ ሲሆን፣ የፌዴራል የስነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለጹት ኮሚሽኑ ያቀደውን





አብዛኛውን ስራ አከናወኗል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በቀረበው ሪፖርት 8 የሙስና መከላከል ጥናቶች ተካሂደው በርካታ ተቋማት በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን፣ በተከናወኑ 15 የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራዎች ከ445 ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ከብክነት ማዳን ተችሏል። በተጨማሪም የሀብት ምዝገባ ስራ ሙሉ በሙሉ ከወረቀት ወደ ዲጂታል ስርዓት (EARS) ተሸጋግሯል።

በመድረኩ ላይ አስራ አንዱም ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የየራሳቸውን የስራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅርበዋል።

ወደ ገጽ 3 የዞረ

# የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በ2019 በጀት ዓመት እቅድ ላይ ውይይት አካሄዱ









የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በ2019 በጀት ዓመት በሚፈጸሙ ዋና ዋና ተግባራት ላይ ውይይት አካሂደዋል:: በውይይቱ፣ በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ፕሮግራም ሥር የሥልጠና፣ የሕዝብ ግንዛቤ ማስጨበጫ እና የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈጻሚዎች ንዑስ ፕሮግራሞች ዕቅድ ቀርበዋል::

በተጨማሪም፣ በሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ፕሮግራም ሥር የሙስና መከላከል ጥናት፣ የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት መከላከል እንዲሁም የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ንዑስ ፕሮግራሞች ዕቅዶች ቀርበው በዝርዝር ተወያይተውባቸዋል:: በፀረ-ሙስና ትብብር ማጎልበቻ ፕሮግራም ሥር የፀረ-ሙስና ዓለም አቀፍ ትብብር ማጎልበቻና የዲጂታል ሙስና መረጃ አስተዳደር ንዑስ ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም በአስተዳደር ድጋፍ አገልግሎት ፕሮግራም ሥር የተቋም አቅምና ብቃት ማሻሻል እና የሥራ አመራርና አስተዳደር አገልግሎት ንዑስ ፕሮግራሞች ዕቅዶችም ቀርበዋል::

በአጠቃላይ፣ አራት ፕሮግራሞችና አስር ንዑስ ፕሮግራሞችን ያካተቱት የ2019 በጀት ዓመት ዕቅዶች መነሻ ተደርገው በተካሄደው ውይይት ከተሳታፊዎች ጥያቄዎች፣ አስተያየቶችና ሀሳቦች ተነስተው በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል:: በመድረኩ የተገኙት የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነሮችም በ2018 በጀት ዓመት የታዩ ጠንካራ ጎኖችንና ክፍተቶችን መነሻ በማድረግ፣ በ2019 በጀት ዓመት ትኩረት ተደርጎባቸው መሠራት በሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ሰጥተዋል::

# የሙስና ወንጀልን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ሁሉም የበኩሉን ሚና ሊወጣ ይገባል - ፍትሕ ሚኒስቴር



የሙስና ወንጀልን በዘላቂነት ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ሁሉም የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል ሲል ፍትሕ ሚኒስቴር አሳወቀ:: በሚኒስቴሩ የሙስና ወንጀሎች ዳይሬክተር ምስክር ታሪኩ እንዳሉት፣ በ2018 በጀት ዓመት ከ1 ሺህ 600 በላይ የሙስና ወንጀል መዝገቦች ተመርምረው ከ300 በላይ ክሶች ተመስርተዋል:: በዚህም ከ400 በላይ ተከሳሾች በፍ/ቤት ቀርበው እንዲቀጡ መደረጉን ጠቁመው፣ በተጠቀሱት መዝገቦች ውስጥ አንድ መዝገብ እስከ 30 እና 40 ተከሳሾችን ሊያካትት እንደሚችል ተናግረዋል::

በሒደቱ የተወሳሰቡ የሙስና ወንጀል ጉዳዮችን በማጣራት ተገቢው ውሳኔ መስጠት መቻሉን ነው ዳይሬክተሩ የገለጹት:: ከተመረመሩት መዝገቦች ውስጥ ከ300 በላይ በሚሆኑት ላይ ክስ የመመስረት ሥራ መከናወኑን አንስተው፣ የሙስና ወንጀሎችን በሕግ አግባብ ወደ ፍርድ ሒደት የማስገባት ሥራ መሰራቱን አብራርተዋል:: ይህም የሙስና ወንጀልን በሕግ ለመቆጣጠር እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የተወሰደውን ርምጃ እንደሚያሳይ አመልክተዋል::

ሙስናን መከላከልና መቆጣጠር የአስፈጻሚ አካላት ኃላፊነት ብቻ እንዳልሆነ ጠቁመው፣ የሕግ አውጪው ተገቢውን ሕግ በማውጣት፤ የሕግ ተርጓሚው ደግሞ ሕጉን በተገቢው መንገድ በመተርጎምና በማስፈጸም የሙስና ትግሉን ማጠናከር እንደሚገባ አስረድተዋል:: የሙስና ወንጀልን በመከላከል፣ በመመርመርና ተጠያቂነትን በማስፈን ሒደት ሁሉም የሕግ ተቋማት ተገቢውን ትኩረትና ኃላፊነት በመውሰድ በጋራ መስራት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል::

## የኮሚሽን የብር ኢዮቤልዩ.. ከገጽ 1 የዞረ



በትውልድ ግንባታና ስልጠና ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ከ2 ሚሊዮን በላይ ዜጎች እና 298 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ስልጠና ማግኘታቸውን በአቶ የኂላእሸት ደሳለኝ ባቀረቡት የመወያያ ሠነድ ላይ ገልፀዋል:: በሀብት ምዝገባ ባለፉት 25 ዓመታት ውስጥ ከ1.5 ሚሊዮን በላይ ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና የመንግስት ሰራተኞች ሀብታቸውን አስመዝግበዋል:: ከ9,000 በላይ የሙስና መከታተያ ሰራተኞች የተሰማሩ ሲሆን፣ በቀጣይም የፀረ-ሙስና ግንዛቤን በቤተሰብ ደረጃ ማውረድ የሚያስችል እቅድ መያዙን ገልጸዋል::

ከተሳታፊዎች በኩል የኮሚሽኑን የሰው ሀይል አደረጃጀት ፍልሰትን ለመቀነስ በጥናት ሊፈተሸ እንደሚገባ፣ የክትትል ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው፣ የኮሚሽኑን



የመፈፀም አቅም ከዚህ በላቀ ማጎልበት እንደሚገባ እና መሰል አስተያየቶች ቀርበዋል::

ለተነሱት ነጥቦች ምላሽ የሰጡት የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቱ አስፋው እና ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኮሚሽኑ በበትውልድ ሥምግባር ግንባታ ስልጠና ላይ በስፋትና በጥራት መስራቱን፣ በሙስና መከላከል ሰፋፊ ተግባራትን ማከናወኑን እና በሙስና መረጃ ማመንጨት ከሌላው ጊዜ በበለጠ መከናወኑን ገልጸዋል:: በተጨማሪም ከገለልተኝነት ጋር በተያያዘ በምርመራና በጥናት ስራዎቹ ላይ ምንም አይነት ጣልቃ ገብነት እንደሌለበትና ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን አረጋግጠዋል::



# በስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል በ2018 በጀት ዓመት የላቀ ውጤት መመዝገቡ ተገለፀ



የአዲስ አበባ ከተማ የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2018 በጀት ዓመት በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተግባራት ላይ በተከናወኑ ስራዎች የላቀ ውጤት መመዝገቡን አስታውቋል:: የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ እና ስኬታማ ለማድረግ ህብረተሰቡን ባማከለ መልኩ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተለያየ መድረክ ማሳተፍ እንደተቻለ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ክቡር አቶ ጀማል ረዲ ገልጸዋል::

በበጀት ዓመቱ በደረጃው ያሉ የመከታተያ ክፍሎችን በተለያዩ ጊዜያት ድጋፍና ክትትል በማድረግ እንድሁም ተገቢውን ምዘና በማካሄድ እና የማብቃት ስራ ለመስራት ጥረት መደረጉን የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አቶ ሃብታሙ ፈይሳ ገልፀው፣ የሃብት ምዝገባ እና ትክክለኛነትን የማረጋገጥ ተግባር ቴክኖሎጅን በመጠቀም ለመስራት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ም/ኮሚሽነሩ ተናግረዋል:: የማህበረሰቡን ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሳደግ ለፀረ-ሙስና ትግሉ አጋዥ ሃሎችን ለማበራከት ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሚገኝ የኮሚሽኑ ፅህፈት ቤት ሃላፊ አቶ ፈቱ ሰማን ገልጸዉ የሰራተኛውን የሙያና የተቋማዊ አቅም ለማሳደግም የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ረገድ በቀጣይ በትኩረት እንደሚሰራ አብራርተዋል::

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከ 13 ተቋማት ጋር የስምምነት ሰነድ ተፈራርሞ ወደ ስራ መገባቱን፣ በተለያዩ መድረኮች ለ1.6 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፈጠሩን፣ ለ204,060 አመራሮች፣ ለመንግስት ሰራተኞችና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስልጠና መሰጠቱን፣ የ57,812 አመራርና ባለሙያዎች ሃብት መመዝገቡን፣ 16 የሙስና ተጋላጭነት ጥናት መሰራቱን፣ በመደበኛና በአስቸኳይ ሙስና መከላከል በገንዘብ 706,630,383.76 ብር ማዳን መቻሉን፣ በብልሹ አሰራርና በስነ ምግባር ችግር ውስጥ የተገኙ 1917 አመራርና ባለሙያዎች ላይ እርምጃ መወሰዱን እና 1822 የሙስና ወንጀል ጥቆማ ቀርቦ መተንተኑን በኮሚሽን ሪፖርት ተመላክቷል::

# በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 4ኛው መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሥራ ጀመረ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 4ኛው የበለስ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት በዛሬው ዕለት ተመርቆ ሥራ ጀምሯል::

የክልሉ ም/ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታሁን አብዲሳ ማዕከሉን በመረቁበት ወቅት እንዳሉት፥ መሶብ የአንድ ማዕከል የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን በማሻሻል የዜጎችን እንግልት የሚያስቀር ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነው::

የበለስ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት በክልሉ አራተኛው ማዕከል መሆኑን ገልጸው፤ የቤጉ መሶብ፣ የአሶሳ እና የባምባሲ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ቀደም ሲል ወደ ሥራ መግባታቸውን አስታውሰዋል:: በክልሉ በተዘረጋው ዘመናዊ የአገልግሎት ስርዓት እስካሁን በ124 የአገልግሎት



ዘርፎች ከ53 ሺህ 900 በላይ ዜጎች የዲጂታል አገልግሎት ማግኘታቸውን ገልጸዋል::በዚህም የእርካታ ደረጃውን 99 ነጥብ 2 ከመቶ ማድረስ ተችሏል ብለዋል::

የመንግሥት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በቴክኖሎጂ በሥርዓት ወደሚመራ ተቋማዊ ብቃት ለመሸጋገር መሶብ አንዱ ማሳያ መሆኑን አንስተዋል::

# በሴኔጋል ባለስልጣናት ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ የሚያስገድደው ህግ ፀደቀ

የሴኔጋል ብሔራዊ ምክር ቤት የፕሬዚዳንቱን፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን እና የብሔራዊ ምክር ቤት ፕሬዚዳንቱን ስልጣን በለቀቁ ጊዜ ሁለተኛ የሀብት ማስታወቂያ እንዲያቀርቡ የሚያስገድድ ህግ አጽድቋል:: ይህ ማሻሻያ ቀደም ሲል ስልጣን ሲይዙ ብቻ ይቀርብ የነበረውን ማስታወቂያ አሁን በስልጣን መጨረሻም እንዲቀርብ በማድረግ በጅምርና በመጨረሻ ያለውን የገንዘብ ሁኔታ ማወዳደር ያስችላል::



በ2001 ጀምሮ የነበረውን የሀብት ማስታወቂያ ደንብ የሚያስፋፋ ሲሆን፣ ባለስልጣናት ስልጣን ከያዙ በኋላ በሶስት ወር ውስጥ እና ስልጣን ከለቀቁ በኋላ ደግሞ በሶስት ወር ውስጥ ማስታወቂያውን ማቅረብ አለባቸው:: ይህ ማሻሻያ (2025) ጀምሮ ተከታታይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል::

ቀደም ሲል ህጉ በከፍተኛ ባለስልጣናት ማለትም የብሔራዊ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ሚኒስትሮች እና ከ1 ቢሊዮን ሲኤፍኤ ፍራንክ በላይ የሚያስተዳድሩ የሂሳብ ሹማምንት ላይ ብቻ ተፈጻሚ ነበር:: የ2025ቱ ማሻሻያ ወሰኑን ከ1 ቢሊዮን ወደ 500 ሚሊዮን ሲኤፍኤ ፍራንክ በመቀነስ አቃቤ ህጎችን፣ የምርመራ ዳኞችን፣ የአካባቢ ተመራጭ ባለስልጣናትን፣ ኦዲተሮችን እና የመንግስት ተቋማት ኃላፊዎችን ጨምሯል:: ህጉን ያለማክበር አሁን ከ6 ወር እስከ 4 ዓመት እስራት፣ የገንዘብ ቅጣት እና ለህዝብ ስልጣን ብቁ አለመሆንን እንደሚስከትል በተለያዩ ሚዲያዎች ተዘግቧል::

## የኮሚሽኖች ትስስር.. ከገጽ 1 የዞረ



በዚህም መሰረት፡ በኦሮሚያ ክልል ሀገር በቀል እውቀትን (የገዳ ስርዓትን) መሰረት ያደረገ አሰራርና ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ ተቋማት ላይ ያተኮረ ስልጠና ተስፋፍቷል:: በአዲስ አበባ 9 የስልጠና ሞጁሎች ተዘጋጅተው ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ከቀረቡ 1,822 ጥቆማዎች 54ቱ ለምርመራና ክስ ተልከዋል:: ከኢንሳ ጋር በመተባበር የዲጂታል ሀብት ምዝገባም ስራ ላይ ውሏል:: በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በአምስት ቋንቋዎች የሚዲያ ግንዛቤ ስራ ተሰርቶ፣ 2 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብና ከ200 ካሬ ሜትር በላይ መሬት ማስመለስ ተችሏል:: በአማራ ክልል ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች የስልጠናና ግንዛቤ ተጠቃሚ ሲሆኑ፣ የኦንላይን ሀብት ምዝገባ በሙከራ ደረጃ ተጀምሯል:: በሲዳማ፣ ሀረሪ፣ ሶማሌ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ጋምቤላ እና ድሬዳዋ ተመሳsሳይ የስነምግባር ግንባታ ስልጠናዎች፣ የሀብት ምዝገባና የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ተግባራት ተከናወናዋል:: በውይይቱ ወቅት አብዛኛዎቹ ክልሎች የስነምግባር ባለሙያዎች የአቅም ውስንነት፣ የሰው ሀይልና የቢሮ ግብዓት እጥረት፣ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ችግርና የመረጃ አያያዝ ክፍተቶችን እንደ ዋና ዋና ፈተናዎች አንስተዋል::

የወደፊት የ2019 በጀት ዓመት አቅጣጫዎችንና የእቅድ ትግበራን በተመለከተ የኮሚሽኑ አመራሮች አስፈላጊውን ማብራሪያና መመሪያ ሰጥተዋል፡

ኮሚሽነር ክቡር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በማጠቃለያው ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ስራ በኋላ ከክልል ኮሚሽኖች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመው፣ ባህላዊ አሰራርን በመተው ዲጂታል ቴክኖሎጂን ታጥቆ መስራት ግድ እንደሚል አጽንኦት ሰጥተዋል:: በሙስና መከላከል ስራ ላይ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ከማስፋት ጎን ለጎን በተቋማት መካከል ጠንካራ ትስስር መፍጠር፣ የተቋማትን ነጻነትና ገለልተኝነት ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን (የሃይማኖት ተቋማትን ጨምሮ) ተሳትፎ ማጠናከር እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል::

የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓቱ መጠናከር እንዳለበት፣ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ በጥናትና ማስረጃ ላይ መመስረት እንዳለበት ምክትል ኮሚሽነር ክቡር እሸቱ አስፋው ገልጸዋል:: የስነምግባር ባለሙያዎች ራሳቸው አርአያ ሊሆኑ እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው፣ አቅዶ የመስራት ልምድን በማዳበር የስራ ግምገማ (Review) ተከታታይነት ባለው መልኩ መከናወን እንዳለበት አሳስበዋል::

የህዝብ ግንዛቤ ስራ ከተጠያቂነት ቀድሞ ሊሰራ እንደሚገባና ማህበራዊ ሚዲያን በብልሃት መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል:: ተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን እንደ "ስነምግባር አምባሳደር" በማየት አቅማቸውን ሊገነቡ እንደሚገባ እና ከኮሌጅ እስከ ታችኛው የትምህርት መዋቅር ድረስ በቅንጅት መስራት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል:: በተጨማሪም የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡ አካላት የሽልማት ፕሮግራም እንደሚኖረው ምክትል ኮሚሽነር ክቡር ፍቃዱ ሰቦቃ አስታውቀዋል::

ጉባኤው የተለዩ የጋራ አቋም መግለጫዎችን በመቀበልና በቀጣይ በጀት ዓመት እቅድ ላይ ስምምነት ላይ በመድረስ ተጠናቋል::

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለህብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

NCRS


# ርዕሰ -አንቀፅ

## የዲጂታላይዜሽን ሚና በፀረ-ሙስና ትግል የተስፋ ብርሃን ወይስ አዲስ የትኩረት አቅጣጫ?

በአሁኑ ወቅት አገራችን ኢትዮጵያ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን እና ግልጽነትን ለማስፈን የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም በስፋት እየተገበረች ትገኛለች:: ዲጂታላይዜሽን አሰራርን ፈጣን እና ቀልጣፋ ከማድረጉ ባሻገር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሙስና እና ብልሹ አሰራር ላይ በሚደረገው ትግል ውስጥ ግንባር ቀደም መሳሪያ በመሆን ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል:: አገልግሎቶችን ዲጂታል ማድረግ (E-governance) የእጅ ንክኪን በከፍተኛ ደረጃ ስለሚቀንስ ለአድልዎና ለጉቦ በር የሚከፍቱ በርካታ ቀዳዳዎችን ይዘጋል:: በተለይም ወረቀት አልባ አሰራር፣ ዲጂታል ክፍያዎች እና የተቀናጁ የመረጃ ቋቶች አሰራርን ግልጽና ተከታታይነት ያለው የዲጂታል አሻራ ያለው በማድረግ ተጠያቂነትን ለማስፈንና ያልተገቡ እንቅስቃሴዎችን በቀላሉ ለመቆጣጠር ያስችላሉ::

ይሁን እንጂ ቴክኖሎጂ በራሱ የመጨረሻ መፍትሔ ሊሆን አይችልም:: ዲጂታላይዜሽን ሙስናን በመከላከል ረገድ ያለው ፋይዳ የጎላ ቢሆንም፣ በሌላ በኩል አዳዲስ የሳይበር ወንጀሎችን እና የዲጂታል አሰራር ቀዳዳዎችን ይዞ የመምጣት የራሱ የሆነ ስጋት አለው:: በመሆኑም ይህንን ዘመናዊ ዕድል በአግባቡ ለመጠቀም እና ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን ለመግታት በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የሚገኙ የፀረ-ሙስና ተቋማት፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲሁም የፍትሕና የሕግ ማስከበር አካላት የተቀናጀና ስትራቴጂካዊ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል:: የቁጥጥር አካላቱ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚዘረጉ የዲጂታል ስርዓቶች ለሙስና አዲስ መንገድ እንዳይከፍቱ አስቀድመው የማረጋገጥና የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው::

ከዚህ በተጨማሪም፣ በዲጂታል መንገድ የሚከናወኑ ትላልቅ የገንዘብ ዝውውሮችን፣ የመንግስት ግዢዎችን እና የአገልግሎት ሂደቶችን በዘመናዊ የሶፍትዌር ቴክኖሎጂዎች ታግዞ የመከታተልና ጥርጣሬ የሚያስነሱ ድርጊቶችን ቀድሞ የመለየት አቅምን በየደረጃው ማጎልበት ይገባል:: ዜጎች ጥቆማዎችንና አቤቱታዎችን ማንነታቸው ሳይገለፅ በምስጢር የሚልኩበትና ክትትል የሚያደርጉበት ደህንነቱ የተጠበቀ የተቀናጀ መተግበሪያ (App/Portal) ማቅረብም ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው:: ይህንንም ስራ ውጤታማ ለማድረግ ህዝቡ መብቱን አውቆ አገልግሎቶችን በዲጂታል መንገድ ብቻ እንዲጠይቅ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራትና በመስመር ላይ የሚፈጸሙ የሙስና ድርጊቶችን ተከታትሎ ለመቅጣት የሚያስችሉ አሰራሮችን ከሳይበር ደህንነት አካላት ጋር በመቀናጀት ማጠናከር ያስፈልጋል::

ባጠቃላይ፣ ዲጂታላይዜሽን ለፀረ-ሙስና ትግሉ ትልቅ እና አስተማማኝ አጋር ቢሆንም፣ ሙሉ ውጤታማ የሚሆነው ግን ጠንካራ የተቋማት አቅም፣ የጸና የፖለቲካ ቁርጠኝነት እና የጠበቀ የተቀናጀ ቁጥጥር ሲታከልበት ብቻ ነው:: በመሆኑም የሚመለከታቸው የፀረ-ሙስና አካላት በሙሉ ከጊዜው ጋር አብረው በመዘመን የቴክኖሎጂውን የበላይነት በመጠቀም ሙስናን ቀድሞ የመከላከል ታሪካዊ ሚናቸውን በተግባር ሊያረጋግጡ ይገባል::



# ቆይታ

## የፀረ-ሙስና ትግል በኢትዮጵያ ካለፉት ሁለት አስርታት

በፀረ-ሙስና ጋዜጣ በዛሬው ቆይታችን የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተመሠረተበትን 25ኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ በዓል ምክንያት በማድረግ፣ የፀረ-ሙስና ትግል በኢትዮጵያ ካለፉት ሁለት አስርታት በላይ ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህ ረጅም ጉዞ ውስጥ ደግሞ ልምድና ትምህርት ሊወሰድባቸው የሚገቡ በርካታ አመራሮች አልፈዋል። ከእነዚህ አመራሮች መካከል አንዱ፣ ከታህሳስ 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 2017 ዓ.ም ድረስ በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በምክትል ኮሚሽነርነት ያገለገሉት አቶ ወዶ አጦ ናቸው። በ12 ዓመታት የአመራር ቆይታቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የሙስና መከላከልና የምርመራና ክስ ስራዎችን ጨምሮ ኮሚሽኑ ሲያከናውናቸው በነበሩ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርገዋል። በኃላፊነት ዘመናቸው ያከናወኗቸውን ዋና ዋና የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራዎች፣ ያጋጠሟቸውን ፈተናዎች እና የተመዘገቡ ስኬቶችን በስፋት ዳስሰዋል። በተጨማሪም ስለ አዳዲስ አዋጆች፣ ዲጂታላይዜሽን፣ ባለድርሻ አካላት ሚና እንዲሁም ለአዲሱ ትውልድና ለተቋሙ አመራሮች ያቀረቡትን ሀገራዊ ጥሪ እና የምክር መልእክት በቃለ-ምልልስ አጠቃልለን አዘጋጅተነዋል። መልካም ንባብ!



**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** በተወካይ በኮሚሽነርነት በዋናነት በምክትል ኮሚሽነርነት በሠሩባቸው ዓመታት የተከናወኑ ዋና ዋና የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል እቅዶች እንዲሁም የተመዘገቡ ስኬቶች ምን ምን ነበሩ? በኃላፊነት ዘመንዎ ያጋጠሙዎት ፈታኝ ሁኔታዎች (challenges) ምን ነበሩ? ሙስናን የመታገል ጉዞው ምን ያህል ፈታኝ ነበር?

**የቀድሞው ምክትል ኮሚሽነር የተከበሩ ወዶ አጦ:-** ከታህሳስ 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 2017 ዓ.ም ድረስ በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በምክትል ኮሚሽነርነት አገልግያለሁ። በቆይታዬ ኢትዮጵያንና ኮሚሽኑን በማገልገሌ በጣም ደስተኛ ነኝ። ሕዝቡና መንግሥት የሰጡኝን አደራ አቅሜ በፈቀደው መጠን በታማኝነትና በቅንነት ለማገልገል ሞክሬለሁ። በመጨረሻም የአገልግሎት ጊዜዬን ጨርሼ "ለሁሉም ጊዜ አለውና' በክብር የተሰጠኝን ሥልጣን አስረክቤ በጡረታ በመውጣቴ ዕድለኛ ነኝ የሚል እምነት አለኝ።

በምክትል ኮሚሽነርነት ባገለገልኩባቸው ዘመናት በአጠቃላይ ከአመራር ቡድኑ ጋር በመሆን ሰፋፊ የሆኑ የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል እቅዶችን ወደ ተግባር ስንተረጉም ቆይተናል።

ከእቅዶቹ መካከል በዋናነት የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ:- በፀረ-ሙስና ትግል ዙሪያ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንዛቤ አድጎ፣ ሙስናን የማይሸከምና በትግሉ ጠንካራና የተደራጀ ተሳትፎ የሚያደርግበትን ሁኔታ መፍጠር ነበር። ዲጂታል ሚዲያ ከመስፋፋቱ በፊት ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚመጥኑ የማስተማሪያ ሞጁሎችን በማዘጋጀት፣ በሞጁሎቹ ዙሪያ የፊት ለፊት ስልጠናዎችን ሰጥተናል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ዜጎችን በማሰልጠን፣ እነሱ ደግሞ ተመልሰው ሌሎችን የሚያሰለጥኑበትን የአሰልጣኞች ስልጠና (ToT) በተከታታይነትና በስፋት ለመስጠት ተሞክሯል።

• ሕትመቶችና የሚዲያ ፕሮግራሞች:- በሕትመት ሚዲያ በኩል በየጊዜው ብሮሸሮችን፣ መጽሔቶችንና የተለያዩ መልእክቶችን በአማርኛና በእንግሊዘኛ በማዘጋጀት ለሕዝቡና ለኤምባሲዎች እንዲደርሱ ተደርጓል። በተጨማሪም ከኢቢሲ (EBC) እና ከፋና (FBC) ጋር በመተባበር በምርመራ ሂደትና በፍርድ ውሳኔዎች ላይ ያተኮሩ አስተማሪ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ሕዝቡ እንዲማርበትና ከወንጀል ድርጊት እንዲጠነቀቅ ተደርጓል።

• የአሰራር ሥርዓት ጥናት (መከላከል):- በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በሕዝባዊ ተቋማትና በልማት ድርጅቶች ለብልሹ አሰራርና ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን በመፈተሽ፣ ክፍተቶችን በመለየትና የችግሩን መፍትሔ የሚጠቁሙ ምክር ሀሳቦችን በማቅረብ እንዲተገበሩ ተደርጓል።

• የሕዝብ ክንፍና የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር:- ኮሚሽኑ ብቻውን የትም መድረስ እንደማይችል በማመን በተቋማት ውስጥ ያሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን፣ የሙያና ህዝባዊ ማህበራትን ማለትም የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የሙህራን፣ የጤና ባለሙያዎችና የሃይማኖት ተቋማትን አቅም የመገንባት ሥራ ተሰርቷል። ከእነዚህ አደረጃጀቶች ጋር በሃገር አቀፍ ደረጃ በየሁለት ዓመቱ ጠቅላላ ጉባኤ የሚካሄድና አጠቃላይ አቅጣጫ የሚቀመጥበት ሲሆን፣ በየስድስት ወሩና በየሦስት ወሩ ደግሞ የሥራ አስፈጻሚ ውይይትና ግምገማ በማድረግ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴውን የሚያስቀጥሉ ተግባራት ሲከናወኑ ነበር።

• የምርመራና ክስ ሥራዎች (እስከ 2008 ዓ.ም):- ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ከግንቦት 16 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን የመቀበል፣ የመመርመርና ክስ የመመስረት ሙሉ ሥልጣን ነበረው። በወቅቱ በርካታ የወንጀል ተጠርጣሪዎች የተከሰሱበት፣ ጥፋተኞች ወደ ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ የተደረገበት እና የተዘረፉ የመንግሥትና የሕዝብ ሀብቶች የተመለሱበት ሥራ ተሰርቷል። በተለይም ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደውን ከፍተኛ የመሬት ወረራ በመታገል ረገድ በሙስና የተሳተፉ አካላት ለሕግ እንዲቀርቡ ተደርጓል። (ከ2008 ዓ.ም በኋላ የምርመራ ሥራው ወደ ፌዴራል ፖሊስ፣ የክስ ሥራው ደግሞ ወደ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ/ፍትሕ ሚኒስቴር መተላለፉ ይታወሳል)።

• ዓለም አቀፍና ቀጣናዊ ግንኙነት:- ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (UN-CAC) እና የአፍሪካ ሕብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽኖች ፈራሚ እንደመሆኗ መጠን የሃገሪቱ የፀረ-ሙስና አፈጻጸም በተመለከተ ሁለት ዙር የአፈጻጸም ግምገማዎች አካሂዳለች። በምሥራቅ አፍሪካ የፀረ-ሙስና ተቋማት ማህበር (EAAA-CA) እና ARIN-EA በተባሉት ቀጣናዊ አደረጃጀቶች ውስጥ ኢትዮጵያ በፕሬዝዳንትነትና በሥራ አስፈጻሚነት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክታለች።

ያጋጠሙ ትልልቅ ፈተናዎች (Challenges):-

የአጀንዳው ባህሪና ውስብስብነት:- ሙስና ከተራ ወንጀል ይለያል፤ በጥናት፣ በእውቀትና በተደራጀ ትስስር የሚፈጸም ሀገር ገዳይ ወንጀል ነው። ድንበር ተሻጋሪ ባህሪ ያለው በመሆኑ ሂደቱ እጅግ ውስብስብና ፈታኝ ነበር።

1.የሕዝብ ተሳትፎ ክፍተት:- ሕዝቡ ውጤት ይፈልጋል፤ ነገር ግን ጥቆማ በመስጠት፣ አጋልጦ በመስጠትና መጥቶ በመመስከር ረገድ የሚጠበቀውን ያህል ተሳትፎ አልነበረዉም። ጉቦ ተቀባይ የሚኖረው ጉቦ ሰጪ ሲኖር ነው። ሕዝቡ "መብቴን በገንዘብ አልገዛም" ብሎ በጽናት ካልታገለ ጉቦኝነትን ማስቆም ከባድ ነው።

2.የቅንጅት ችግር:- በፌዴራል የፍትሕ ተቋማት (በኮሚሽኑ፣

በፖሊስና በፍትሕ ሚኒስቴር) መካከል፣ እንዲሁም በፌዴራልና በክልሎች መካከል የነበረው ቅንጅትና መናበብ ጠንካራ አልነበረም።

3.የ2008 ዓ.ም የመዋቅር መቀየርና የተቋሙ ስም መበላሸት፡- በ2008 ዓ.ም የምርመራና ክስ ሥልጣን ወደ ፖሊስና ፍትሕ ሚኒስቴር እንዲዛወር ሲታሰብ፣ ኮሚሽኑ ምንም እንደማይሰራ ተደርጎ ስሙ እንዲበላሽና ጥላሸት እንዲቀባ ተደርጓል። ይህም ካለአግባብ የተከናወነና እጅግ ያሳዘነኝ ክስተት ነበር። ኮሚሽኑ ሲገለገልበት የነበረዉን ቢሮ ፍትሃዊነት በጎደለዉ መንገድ ለቆ እንዲወጣ ከተወሰነ በኋላ ሰራተኛው ተረጋግቶ ስራዉን የሚሰራበት ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ ኮሚሽኑ ከፍተኛ ጫና ዉስጥ ወድቆ የነበረበት ሁኔታ ነበር።

4.የአመራርና የባለሙያ አቅም ውስንነት፡- ከጊዜው ጋር የሚሄድ የምርመራ ቴክኒክ፣ የክስ አቅምና የማስተማር ብቃት ማደግ ነበረበት። የአመራሩና የባለሙያው አቅም ከሕዝቡ ፍላጎት አንጻር ሲታይ ውስንነቶች ነበሩበት።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በቅርብ ጊዜያት የወጡ አዳዲስ የፀረ-ሙስና ሕጎች እና መመሪያዎች በርስዎ በነበረው አሰራር ላይ ያመጡት ለውጥ አለ? የሀብት ምዝገባ ሕግ እንዲሁም የመንግሥት አሰራር ግልጽነትን ለማረጋገጥ የተወሰዱ እርምጃዎች ውጤታማነት ላይ የእርስዎ ግምገማ ምንድን ነው?

**የቀድሞው ምክትል ኮሚሽነር የተከበሩ ወዶ አጦ፡-** የፀረ-ሙስና ትግል የትውልድ ቅብብሎሽ ሂደት ነው። በ2013 ዓ.ም የወጣው ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ለኮሚሽኑ በጣም ሰፊ ሥልጣን ሰጥቷል። ቀደም ሲል አሰራሩ በመንግሥታዊ ተቋማት ላይ ብቻ የተገደበ የነበረ ቢሆንም፣ አዲሱ አዋጅ ግን በግል ሴክተሩም ውስጥ ገብቶ የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን ለመስራት መንገድ ከፍቷል።

በተጨማሪም አዋጁ የቅንጅት ችግርን የሚቀርፍ አሰራር ዘርግቷል። ፖሊስ የሚያካሂደውን የምርመራ ሥራ፣ ፍትሕ ሚኒስቴር ደግሞ የሚያካሂደውን የክስ ሥራ ለኮሚሽኑ ሪፖርት እንዲያደርጉ ሕጉ ያስገድዳል። ኮሚሽኑ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ የፀረ-ሙስና ትግሉ ዋና አስተባባሪ (Focal Point) ሆኖ እንዲሠራ ሕጋዊ መሠረት ጥሏል። አሁን ባለው ሁኔታ በፍትሕ፣ በፖሊስና በኮሚሽኑ መካከል ያለው ቅንጅትና መናበብ እጅግ እየተሻሻለ መምጣቱ የሚያስደስት ነው።

ሌላው ትልቅ ለውጥ ዲጂታላይዜሽን ነው፡- የጥቆማ አቀባበል ቀደም ሲል ጠቋሚዎች በአካል ቢሮ መመላለስ ነበረባቸው፤ አሁን ግን በተዘጋጁ አፕሊኬሽኖች አማካይነት ማንነታቸው ሳይገለጥና የበቀል እርምጃ ሳይፈሩ ባሉበት ሆነው በጥቆማ መተግበሪያዎች ጥቆማ መስጠት የሚችሉበት አሰራር ተዘርግቷል፣ የሀብት ምዝገባ ቀደም ሲል በጽሑፍ (ማኑዋል) ይካሄድ የነበረው አሰራር ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ በከፍተኛ ሁኔታ የሚወስድ ነበር። አሁን በዲጂታል መንገድ መሆኑ ባለሥልጣናትና ተሿሚዎች ባሉበት ሆነው ሀብታቸውን በቀላሉ እንዲያስመዘግቡና እንዲያሳውቁ ዕድል ፈጥሯል እና የሥነምግባር ግንባታ ስልጠናዎችን በዲጂታል ሚዲያ፣ በዩቲዩብና በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ማድረስ ተጀምሯል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በአሁኑ ወቅት በአገራችን የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ እና ዲጂታላይዜሽን (Digitalization) ላይ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷል። ዲጂታል አሰራር ሙስናን በመከላከል ረገድ ያለው ሚና እንዴት ይታያል?

**የቀድሞው ምክትል ኮሚሽነር የተከበሩ ወዶ አጦ፡-** ዲጂታል አሰራር እጅግ ወሳኝና ዘመናዊ ነው። ኢትዮጵያ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ስትራቴጂን ለማሳካት እቅድ አላት። በዚህ ፈጣን የለዉጥ ዘመን ዉስጥ የፀረ-ሙስና ትግሉም ከዘመኑ ጋር አብሮ መሮጥ አለበት።

ዲጂታል አሰራር ጊዜን፣ ገንዘብንና ጉልበትን የሚቆጥብ ከመሆኑም በላይ ግልጽነትን ያረጋግጣል። ለምሳሌ አሁን የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስ ግዥ (e-Procurement) አሰራር ከፍተኛ ሙስና ይፈጸምበት የነበረውን የመንግሥት ግዥ ሂደት ግልጽና ከሙስና የፀዳ እንዲሆን ለማድረግ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

በአጠቃላይ ሙስናን ለመከላከል በአንድ በኩል በሰው አእምሮ ላይ በመስራት አስተሳሰብን መቀየር ያስፈልጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ አሰራራችንን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ ማድረግ ይገባል። ሁለቱ ከተቀናጁ ውጤቱ እጅግ የበረታ ይሆናል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በቅርቡ በአንዳንድ ተቋማት የሚስተዋሉ የሥነምግባር ጉድለቶችን እና የሙስና ስጋቶችን ለመቀነስ የሕዝብ ተሳትፎ እና የባለድርሻ አካላት ድርሻ ምን መሆን አለበት ብለው ያምናሉ?

**የቀድሞው ምክትል ኮሚሽነር የተከበሩ ወዶ አጦ፡-** ሙስና የአንድ ተቋም ወይም የግለሰብ አጀንዳ ሳይሆን የአገር አጀንዳ ነው። የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የማስተባበር ሚና ቢኖረውም፣ ትግሉ የሁላችንም አጀንዳ መሆን አለበት።

ባለድርሻ አካላት ሊወጡት የሚገባ ሚና፡- ሕዝቡ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት መሆኑን በተግባር ማረጋገጥ አለበት። ሕጋዊ አገልግሎት ለማግኘት ጉቦ መስጠት የለበትም፤ "አገልግሎት ሰጪዉ ደሞዝ የሚከፈለዉ ዜጎች በሚከፍሉት ግብር ነዉ። ስለሆነም ዜጎች አገልግሎት የማግኘት ተፈጥሯዊ መብታቸዉን በገንዘብ መግዛት የለባቸዉም። "ጉቦ አልሰጥም" የሚል ጠንካራ አቋም መያዝ አለበት። ሚዲያው መደበኛ ዜና ከመዘገብ አልፎ የመርማሪ ጋዜጠኝነትን (Investigative Journalism) በማጠናከር የማህበረሰቡን ንቃት ማሳደግ አለበት። የሃይማኖት ተቋማት ምዕመናኖቻቸውን እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ የሕዝብና የአገር ሀብት የማይሰርቁና ለእውነት የሚቆሙ እንዲሆኑ የማስተማር ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። የሃይማኖት አባቶችም በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባር አርአያ መሆን አለባቸው። የትምህርት ሥርዓቱ ትውልድን በሥነምግባር የመቅረጽ ሥራ ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምሮ በስርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ ተካቶ ሊሰራበት ይገባል። በመንግሥት በኩል በተግባር የሚገለጽ ጠንካራ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ሊኖር ይገባል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በአሁኑ ወቅት የፀረ-ሙስና ትግሉን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ አሁን ባለው የኮሚሽኑ አወቃቀር እና አሰራር ላይ ምን አይነት ማሻሻያዎች መደረግ አለባቸው ይላሉ?

**የቀድሞው ምክትል ኮሚሽነር የተከበሩ ወዶ አጦ፡-** አሁን ባለው ሕግ የኮሚሽኑ ሥልጣን ሰፊ ነው፤ አወቃቀሩም ቢሆን ወደፊት በየጊዜው የሚፈተሽ ቢሆንም አሁንም ቢሆን ብዙ ርቀት ሂደው እንዲሠሩ ዕድል ይሰጣል።

ዋና ዋና ማሻሻያዎች፡- ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ፖሊሲን ማጽደቅ፡- በቅርጽ ደረጃ ያለው ብሔራዊ የፀረ-ሙስና መከላከል ፖሊሲ ጸድቆ ወደ ሥራ መግባት አለበት። የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አጀንዳዎች፡- ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከሚቀርቡት አጀንዳዎች መካከል አንዱ የሙስና ጉዳይ በመሆኑ፣ በሂደቱ መጨረሻ ላይ የሚቀርቡትን የመፍትሔ ሀሳቦችና ምክረ-ሀሳቦች በአግባቡ መጠቀምና መተግበር ያስፈልጋል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በአሁኑ ወቅት በተቋሙ ለሚሰሩ አመራሮች እና ባለሙያዎች፣ እንዲሁም ለወጣቱ ትውልድ የሥነምግባር ግንባታን በተመለከተ የሚያስተላልፉት መልእክት ወይም ምክር ምንድን ነው?

**የቀድሞው ምክትል ኮሚሽነር የተከበሩ ወዶ አጦ፡-** ለወጣቱ ትውልድ፡- ወጣቶች የአገር ተረካቢዎች ብቻ ሳይሆኑ የአገር መሪዎችም ናቸው። በአቋራጭ የመበልፀግና የመክበር አስተሳሰብ አገር አጥፊ እንጂ አገር አሻጋሪ አይደለም። ወጣቱ በሥራና በሥራ ክብር ማመን፣ በራሱ ጥረትና እውቀት ሀብት ማፍራት እንደሚቻል አምኖ በአቋራጭ የመበልፀግ አስተሳሰብን ሊታገል ይገባል። ለኮሚሽኑ ባለሙያዎች፡- በሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ውስጥ ሰራተኛ ሆኖ መስራት ትልቅ ዕድልና ኃላፊነት ነው። ሌሎችን "ሌብነትና ሙስና አታድርጉ" ብለን ስናስተምር እኛ ከዛ ነገር የፀዳን መሆን አለብን። በተግባር አርአያና ሞዴል ተቋም ሆነን መውጣት ይኖርብናል።

ለኮሚሽኑ አመራር፡- አመራሩ ሀገራዊ ሁኔታውን በመረዳት መከላከልን ማዕከል ያደረጉ ስትራቴጂዎችን መንደፍና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን (መንግሥትን፣ ሚዲያን፣ ክልሎችንና የሥነምግባር ክፍሎችን) ማስተባበር አለበት፤ ፈጣን ለውጦችን መሸከም የሚችል ተከታታይነት ያለው የአመራርና የባለሙያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት ይገባል፤ ከክልሎች ጋር ያለውን ቅንጅት ማጠናከር አለበት፤ መልካም ሥነምግባር ያላቸውን አመራሮችና ባለሙያዎችን የመለየትና የመሸለም (የእውቅና አሰጣጥ) ፕሮግራሞችን ማጠናከር ያስፈልጋል እንዲሁም ዓለም አቀፍና ቀጣናዊ (እንደ EAAACA እና ARIN-EA ያሉ) ትስስሮችን በማጠናከር ቴክኒካዊና የመረጃ ልውውጥ ድጋፎችን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል።

በአጠቃላይ፣ አዲሱ አመራርና ትውልድ በጣም ዕድለኛ ነው። የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለ፤ ዲጂታል ቴክኖሎጂው ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፤ ሕዝቡን በአግባቡ መምራትና አቅጣጫ ማሳየት ከተቻለ ከጎናችን ይሰለፋል። እነዚህን ዕድሎች በመጠቀም የፀረ-ሙስና ትግሉን ማጠናከር ያስፈልጋል።

**እናመሰግናለን!**

# ሳይቃጠል በቅጠል

## የ17ኛው ሀገር አቀፍ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ የጋራ አቋም መግለጫ

ሙስና እየተወሳሰበና እየከበደ የመጣ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ችግር በመሆኑ፣ በአንድ ተቋም ብቻ ሊፈታ አይችልም። ስለሆነም የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ መንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት፣ የፍትህ አካላት፣ ህብረተሰቡና ሌሎች ባለድርሻዎች በትብብርና በቅንጅት መሥራት ይገባል። በመሆኑም የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ግልጽና የተሻሻለ አሠራር፣ ጠንካራ ትብብር፣ የመረጃ ልውውጥና ቅንጅት ማጠናከር ወሳኝ መሆኑን በአፅንኦት እንገነዘባለን።

በ17ኛው ሀገር አቀፍ የትስስር ጉባኤ የ2018 በጀት ዓመት አፈፃፀምና የ2019 የአንድ ዕቅድ፣ አንድ ሪፖርት አቅጣጫ በጋራ ተገምግሟል። በ2018 ዓ.ም. 26 ዘርፍ ተኮር የሥነ-ምግባር ሥልጠና ሞጁሎች ተዘጋጅተው ለ248,853 አመራሮችና ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፤ ለ33,852,875 ዜጎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡፡ ከ10,000 በላይ የሥነ-ምግባር መከታተያ ባለሙያዎች ተደራጅተዋል። በተጨማሪም ከ77 በላይ የሙስና መከላከል ጥናቶችና በሺዎች የሚቆጠሩ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራዎች ተከናውነዋል። በዚህም በቢሊዮን የሚቆጠር ብርና በሺዎች የሚገመት የከተማና የገጠር መሬት ከብክነት ማዳን ተችሏል። እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠሩ ጥቆማዎች ለምርመራ ተላልፈዋል፡ ፡ የተቋማት አቅምን፣ አደረጃጀትን፣ አሠራርንና ሕግን የማሻሻል ሥራዎችም ተከናውነዋል።

እነዚህ ውጤቶች በፀረ-ሙስና ትግሉ መሻሻል መኖሩን የሚያሳዩ በመሆናቸው፣ የተገኙ ጥንካሬዎችን በማስቀጠል፣ የታዩ ክፍተቶችን በማረምና ትብብርና ቅንጅትን በማጠናከር የፀረ-ሙስና ትግሉን ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ለማስቀጠል ቁርጠኛ ነን።

በዚሁ መሠረት፦

በተቋማት ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሠራር እንዳይከሰት የአመራሮችና የሠራተኞችን የሥነ-ምግባር ግንዛቤ ማሳደግ ወሳኝ ነው። በመሆኑም የሥነ-ምግባርና የሙስና መከላከል ሥልጠናዎችን በስፋት በመስጠት ተገቢ የሥነ-ምግባር ባህልን እናጠናክራለን።

የፀረ-ሙስና ትግል ውጤታማ የሚሆነው ህዝቡ ችግሩን በመረዳትና በትግሉ በንቃት ሲሳተፍ ነው። ስለሆነም በመረጃና በማስረጃ የተደገፉ የግንዛቤ መልዕክቶችን በተለያዩ ሚዲያዎች በማሰራጨት የህዝብን ተሳትፎ እናሳድጋለን።

ከ10,000 በላይ የሥነ-ምግባር መከታተያ ባለሙያዎችን በትስስር በማደራጀትና የተቋማትን አደረጃጀት በማጠናከር የሥነ-ምግባር አፈጻጸም በተገቢው ሁኔታ እንዲከናወን በማድረግ በመንግስት ተቋማት እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ችግሮችን በጊዜ ለይቶ የመፍታት አቅምን በማሳደግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር ቃል እንገባለን!

ሙስና ሊከሰትባቸው የሚችሉ ስትራቴጂካዊና ተጋላጭ አሠራሮችን በጥናት በመለየት የመከላከያ መፍትሔዎችን በማመንጨት የሚቀርቡ የማሻሻያ ምክረ-ሐሳቦች በተቋማት ተግባራዊ እንዲሆኑ የላቀ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ቃል እንገባለን!

ከህዝብ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን በፍጥነት በመለየት በተለይ ሙስና ከመፈጸሙ በፊት አስቸኳይ የመከላከል እርምጃ በመውሰድ ሙስና ሂደት ላይ ሳለ የማቋረጥ እና የህዝብን ሀብት ከብክነት የማዳን ሥራ በሰፊው ለማከናወን ቃል እንገባለን!!

የአመራሮችና የሠራተኞች ሀብት በትክክል መመዝገቡ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ የሀብት ምዝገባን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ ለማከናወን ቃል እንገባለን!

በሙስና ስጋት የተጋለጡ ዘርፎችና ተቋማት የሀብት መረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ አጠራጣሪ የሀብት ልዩነት ወይም ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ተግተን እንሰራለን!

የህዝብ ጥቆማ የሙስናን ክስተት በጊዜ ለመለየትና ለመከላከል ዋና የመረጃ ምንጭ መሆኑን በመንዘብ የጥቆማ ምስጢራዊነትን በመጠበቅና በቴክኖሎጂ በማጠናከር ጥቆማዎች በተገቢው እንዲመረመሩና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ እናደርጋለን።

የፀረ-ሙስና ትግል የአንድ ተቋም ብቻ ኃላፊነት ስላልሆነ፣ ሁሉም ባለድርሻዎች በተቀናጀ መልኩ መሥራት ይገባቸዋል። በመሆኑም ከመንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት፣ ከፍትህ አካላትና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ትብብርና ቅንጅትን እናጠናክራለን።

የኮሚሽኖች አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ግልጽና ተፅዕኖ ፈጣሪ እንዲሆንየአሠራርናየአደረጃጀት ማሻሻያዎች በየጊዜው በማከናወን ተቋማዊ ሪፎርምን በማጠናከር ውጤታማ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ሥራ እናከናውናለን።

የፀረ-ሙስና ሥራዎች የተቀናጀና የረጅም ጊዜ አቅጣጫ እንዲኖራቸው ሀገራዊ ፖሊሲ መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የሀገራዊ የሥነ-ምግባርና የሙስና መከላከል ፖሊሲ ፀድቆ በተግባር እንዲውል ያለሳለሰ ጥረት እናደርጋለን።

ከዕለት ተዕለት የህዝብ አገልግሎት ጋር የሚያያዙ ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን በመከላከል ፈጣንና ውጤታማ አገልግሎት ማረጋገጥ ይገባል። የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎትን ከዲጂታል የሙስና መረጃ ቅበላ (NCRS) ጋር በማጠናከር የህዝብን አገልግሎትና ተጠያቂነት በላቀ ደረጃ ለማሻሻል ቃል እንገባለን!

በአጠቃላይ በ2018 በጀት ዓመት የተገኙ ጥንካሬዎችን በማስቀጠል፣ የታዩ ክፍተቶችን በማሻሻል፣ ትብብርና ቅንጅትን እንዲሁም የመረጃ ልውውጥን በማጠናከር በ2019 በጀት ዓመት የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴን በተጠናከረ መልኩ ለማስቀጠል ቃል እንገባለን!

ዋና ዓላማችንም ሙስናን ከተፈጸመ በኋላ ብቻ ለመቆጣጠር ሳይሆን፣ ቀድሞ መከላከል፣ የህዝብን ተሳትፎ ማሳደግ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን እና ሁሉንም ባለድርሻዎች በተቀናጀ የፀረ-ሙስና ትግል ማስተሳሰር ነው!!

"ትውልድን በሥነ-ምግባር፣ ተቋምን በአሠራር!'

አዳማ

ነሐሴ/2018

እናመሰግናለን!!!

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

“የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተልዕኮውን ለመወጣት በየጊዜው የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ይገኛል:: ከእነዚህም መድረኮች መካከል በየሁለት ሳምንቱ ለንባብ የሚበቃው ዲጂታል ጋዜጣችን አንዱና ዋነኛው ነው:: ጋዜጣችን ከያዛቸው አበይት ዓምዶች መካከል ‘ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር’ የሚለው ይገኝበታል:: በዚሁ መሠረት በዚህ እትማችን ለህብረተሰቡ ትምህርት ይሰጣሉ ብለን ያመንንባቸውንና በሙስና ወንጀል የተሳተፉ ግለሰቦችን ጉዳይ አስመልክቶ የተዘጋጀውን ዝርዝር መረጃ ለአንባቢዎቻችን አቅርበናል::”

በከባድ የሙስና ወንጀል በተጠረጠሩ 41 የገቢዎች ሚኒስቴር ባለሙያዎች እና ግብረ አበሮቻቸው ላይ ፍርድ ቤት የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ ፈቀደ

ከገቢ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ በከባድ የሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ 41 የገቢዎች ሚኒስቴር ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች እና ተባባሪ ግለሰቦች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ቀርበዋል::

በዛሬው ዕለትም ችሎቱ የተጠርጣሪዎችን ማንነት በማረጋገጥ የግራ ቀኙን ክርክር አዳምጧል::

ፖሊስ የተፈጸመው ወንጀል በመደራጀት የተካሄደ የኢኮኖሚ አሻጥር በመሆኑ ሰፊ እና ውስብስብ መሆኑን ገልጾ የደረሰውን የጉዳት መጠን በኦዲት ለማረጋገጥ እና በቂ ማጣሪያ በማድረግ የምርመራ መዝገቡን አደራጅቶ ለማቅረብ የ14 ቀናት የምርመራ ጊዜ እንዲፈቀድለት ጠይቋል::

የጉዳት መጠኑን በቀጣይ ቀጠሮ ይፋ እንደሚያደርግ የገለጸው ፖሊስ፣ ተጠርጣሪዎቹ በዋስ ቢለቀቁ ምስክሮችን ሊያባብሉ እና ሰነዶችን ሊያጠፉ ስለሚችሉ የዋስትና ጥያቄን ተቃውሟል::

የተጠርጣሪ ጠበቆች በበኩላቸው፣ ፖሊስ ያቀረበው ጥርጣሬ በቂ እንዳልሆነ፣ የተጠረጠሩበት ጉዳይም በጥቅሉ የቀረበ መሆኑን በማንሣት፣ መርማሪ ፖሊስ ይህን ያደረገው ጊዜ ለመግዛት ብቻ ነው ሲሉ ተከራክረዋል::

በተጨማሪም የተጠርጣሪዎችን የጤና ሁኔታ እና የማቆያ ቦታ ጥበትን ምክንያት በማድረግ፣ ደንበኞቻቸው በዋስትና ወጥተው በውጭ ሆነው እንዲከራከሩ ጠይቀዋል::

የግራ ቀኙን ክርክር በዝርዝር ያዳመጠው እና የፖሊስን የምርመራ መዝገብ የተመለከተው ችሎቱ፣ በቂ ጥርጣሬ መኖሩን ከመዝገቡ በመረዳቱ እና የደረሰው የጉዳት መጠን እና የግለሰቦች ተሳትፎን ለይቶ ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘቡን ገልፆ ኢቢሲ ዘግቧል::



በመሆኑም ፖሊስ የጀመረውን ማጣሪያ አጠናክሮ እንዲቀጥል፣ ጉዳያቸው መታየት ከጀመረበት ከሐምሌ 30 እና ነሐሴ 1 ጀምሮ የሚታሰብ የ14 ቀናት የምርመራ ጊዜ ፈቅዷል::

የተጠርጣሪዎችን የጤና ሁኔታ እና አያያዝን በተመለከተ አስፈላጊው ሁሉ እንዲደረግ ትዕዛዝ ተሰጥቷል::

መዝገቡን ለመመልከትም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል:: የፍርዱን ሂደት ተከታትለን ለህዝብ ይፋ የምናደርግ መሆኑን እናሳስባለን::

# መልካም ዜጋ

## የፅዳት ሰራተኛዋ እናት ድንቅ የታማኝነት አርአያነት

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጅጅጋ ከተማ በሚገኘው ጀኸዲን ቅርንጫፍ ውስጥ የተፈጸመው ይህ ድንቅ ታሪክ የሰውን ልብ የሚነካና እጅግ ኩራት የሚሰጥ ነው::

አንዲት የባንኩ የፅዳት ሰራተኛ (እናት) በስራ ገበታዋ ላይ እያለች ደንበኛ ረስቶት የሄደውን ከ12 ግራም በላይ (የዋጋ ግምቱ ከ300 ሺህ ብር በላይ የሚገመት)ወርቅ ታገኛለች:: ወርቁን ወዲያውኑ ለማናጀሩ በማስረከብ፣ የባለቤቱ ፍለጋ ተደርጎ ንብረቱ በሰላም ለባለቤቱ እንዲመለስ አድርጋለች::

ገንዘብ እና ሀብት በጊዜ ሂደት ሊመጡና ሊሄዱ ይችላሉ፤ ነገር ግን ንጹህ ህሊና እና እውነተኛ ታማኝነት በምንም ሊገዙ የማይችሉ ውድ ስብዕናዎች ናቸው:: ይህች የክብር እናት የኢትዮጵያውያንን እውነተኛ የሞራል ከፍታና ውብ መገለጫ በግባር አሳይታናለች:: ለዚህች እናታችን እና ለቅርንጫፍ ማናጀሩ ላሳዩት ስነምግባራዊ መልካም አርአያነት ልባዊ ክብርና ምስጋናችና ቀርቦላቸዋል::

መልካም ዜግነት እና ታማኝነት: ከእናትየዋ አርአያነት የምንወስደው ትምህርት



መልካም ዜግነት በቃላት የሚገለጽ መፈክር ሳይሆን፣ በቀን ተቀን ህይወት በሚደረጉ ትንንሽ እና ትልልቅ ውሳኔዎች የሚገለጥ ተግባራዊ እሴት ነው:: በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የጀኸዲን ቅርንጫፍ የፅዳት ሰራተኛዋ እናታችን ያሳዩት ተግባር የምርጥ ዜግነት ቁልፍ መገለጫዎችን በግልጽ ያሳያል:_

ከቁሳቁስ በላይ ህሊናን ማስቀደም: መልካም ዜጋ ፊቱ ላይ የሚታየውን ስግብግብነት(ጊዜያዊ) ጥቅም ወይም የገንዘብ ችግር ቢኖርበትም እንኳ፣ የሌላውን ሰው ንብረትና ሰብአዊ መብት ያከብራል:: የእናትየዋ ውሳኔ እውነተኛ ሀብት በባንክ የሚቀመጥ ገንዘብ ሳይሆን በቁስ የማይንበረከክ ንጹህ ህሊና መሆኑን ያስመስክራል::

ባለአደራነት እና ተቋማዊ ስነ-ምግባር: መልካም ዜግነት የሚሰራበትን ተቋም እና ማህበረሰብ በቅንነት ማገልገልን ይጠይቃል:: እቃውን ላገኘችበት ተቋም አመራር (ለማናጀሩ) ወዲያውኑ ማስረከቧ፣ ተቋማዊ አሰራርን ማክበር እና የነበረውን እምነት መጠበቅ መሆኑን ያሳያል::

ለማህበረሰብ ሰላም እና እምነት መሰረት መሆን: ማህበረሰብ የሚገነባው በአባላቱ መካከል በሚኖር የእርስ በእርስ እምነት ነው፤ ታማኝነት በጠፋበት ቦታ ሰላምና ህብረት አይኖርም:: ይህች እናት ያሳዩት በጎ ተግባር የሰዎችን ስጋት የሚቀንስ እና በህብረተሰቡ መካከል ያለውን የመተማመን ትስስር የሚያጠናክር ነው::

የአርአያነት ተጽዕኖ: መልካም ዜጋ ለመሆን የግድ ትልቅ ስልጣን ወይም ሀብት ማካበት አያስፈልግም:: ባለንበት ቦታ ሁሉ በታማኝነትና በቅንነት በመስራት የሌሎችን ህሊና ማንቃት እና ለትውልድ የሚሻገር በጎ አርአያነት መተው ይቻላል::

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጀኸዲን ቅርንጫፍ የፅዳት ሰራተኛ ያሳዩትን እውነተኛ ታማኝነት አብነት በማድረግ፣ መልካም ዜግነት በቃላት ሳይሆን በዕለት ተዕለት ተግባር እና በንጹህ ህሊና የሚገለፅ እሴት መሆኑን ያብራራል:: የታማኝነት ተግባሩ ህሊናን ከቁሳቁስ ማስቀደምን፣ ተቋማዊ አደራን ማክበርን፣ የማህበረሰብ መተማመንን ማጠናከርን እና ያለ ትልቅ ስልጣንም ቢሆን ለትውልድ የሚሆን በጎ አርአያ መሆን እንደሚቻል ያረጋግጣል::

# ኪነ-ጥበብ

## ከትውልድ ይሰራ

ከምንጩ ሲቀዳ ንጹህ ከሆነበት፣
ከወንዙማ አይሆንም ድፍርስርስ ካለበት::
መሰረቱ ሲጣል ካልሆነ ከአለቱ፣
ከአሸዋ ከሆነ ጅምር መሰረቱ፣
ምኑን ቤት ሆነና ይኖራል ጽናቱ?
ይፈርሳል ይናዳል ንፋስ በመጣ ዕለት፣
ወጀብ እንዳያፈርሰው ከአለት ላይ ነው መሥራት::
ምግባርም እንዲህ ነው ሲሰራ ከትውልድ፣
ጠንካራ ይሆናል በቀላል ማይናድ::
መሰረቱ ስሩ ከስር ከተሰራ፣
ንፋስ አይወስደውም እንዲሁ በተራ::
ትውልድ ላይ እንስራ በወጣት በህጻናት፣
ከምንጩ ሲቀዳ ይኖረዋል ጥራት::
ከላይ ከሆነ ግን ዋጋ ያስከፍላል፣
ውጤቱም አያምርም ነጥብም ያስጥላል::
ስለዚህ ይመረጣል ከምንጩ ቢቀዳ፣ ቢተከል ከአለቱ፤
ከስሩ ከሆነ ሁልጊዜም ያምራል መልካም ነው ውጤቱ!

ከፈቃዱ በላይ